# የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ መመሪያ

# ቁጥር 142/2013

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም

# የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 142/2013

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. <u>አውጪው ባለስልጣን</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 767/2004 አንቀጽ 5 እና 7/3/ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 20/2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፣

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 142/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ታክስ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 767/2004 መሠረት በጫት ግብይት ላይ የሚከፈል ኤክሳይዝ ታክስ ነው፤
2. "አዋጅ" ማለት ስለጫት ኤክሳይዝ ታክስ የወጣ አዋጅ ቁጥር 767/2004 ነው፤
3. "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፤

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ታክስ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች እና የታክሱ አሰባሰብ</u>

4. <u>ታክሱ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች</u>

1. በጫት ላይ የሚከፈለው ታክስ የሚሰበሰበው ክልሎች በጥናት በመለየት ለባለሥልጣኑ በሚያሳዉቁት ቦታዎች ላይ ብቻ ይሆናል።
2. አግባብነት ያላቸው የክልል የታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በሚለዩዋቸው ቦታዎች ላይ ከመነሻው የጫት ምርት ግብይት የሚካሄድበት፣ የሚደራጅበት እና የሚጫንበት ቋሚ የገበያ ማዕከል በማዘጋጀት ታክሱ በዚሁ ስፍራ እንዲሰበሰብ ያደርጋሉ።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመመካከር እንደሁኔታው ዝርዝሩን ሊያሻሽለው ይችላል።

5. ስለ ታክሱ አሰባሰብ

1. ባለስልጣኑ ታክሱን ለመሰብሰብ በአዋጁ አንቀጽ 6/1 የተሰጠውን ስልጣን በባለስልጣኑ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 6/13 መሠረት የክልል ታክስ ባለስልጣናት በየክልላቸው ከሚገኙ የጫት ምርቱ ከሚነሳባቸው ቦታዎች ታክሱን እንዲሰበስቡ በዚህ መመሪያ ውክልና ሰጥቷል፡፡
2. የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት፡-
   (ሀ) ከመነሻው በጫት አቅርቦት ስራ የተሰማሩ ታክስ ከፋዮችን በግብር ከፋይነት መዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡
   (ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጣቸውን ውክልና መነሻ በማድረግ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት በኪሎ ግራም ብር 5/አምስት ብር/ ሂሳብ እየተሰላ በጫት ግብይት ላይ ታክሱ ከመነሻው እንዲሰበሰብ ያደርጋሉ፡፡
   (ሐ) ክልሎች በአዋጁ አንቀጽ 8 መሠረት በከተሞችና መንደሮች በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ጫት የሚሸጡ ነጋዴዎችን በግብር ከፋይነት በመመዝገብ ፀንተው በሚሰራባቸው ህጎች መሰረት የንግድ ትርፍ፤የተጨማሪ እሴትታክስ ወይም የተርን ኦቨር ታክስ ያስከፍላሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ጫት በዋስትና ስለሚያዝ ቫውቸር አፈፃፀም

6. የቫውቸር ዋነኛ ባህሪያት

ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ጫት ላይ ለሚከፈለው ታክስ ዋስትናነት የሚያገለግለው ቫውቸር፡-

1. የገንዘብ ዋጋ ያለው ይሆናል፡፡
2. ከተፈቀደለት ባለመብት በስተቀር ለሌላ ወገን የማይተላለፍ ነው፡፡
3. የቫውቸሩ ተጠቃሚ የገንዘብ መጠን ጠቅሶ የሚሰጠው ነው፡፡
4. የጫት ላኪዎች በሚያጓጉዙት ጫት ላይ በታክስ መሰብሰብያ ቦታዎች ሊከፈል ለሚገባው ታክስ በዋስትናነት የሚያገለግል ነው፡፡

7. የቫውቸሩ ተጠቃሚዎች

1. በቫውቸሩ መጠቀም የሚችሉት የጫት ላኪነት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው እና የጫት ምርት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ብቻ ናቸው፡፡
2. የቫውቸር ተጠቃሚዎች ቫውቸሩን የጫት ምርቱን ከሚያነሱበት የክልል ታክስ ባለስልጣን ማግኘት የሚችሉት በክልሉ ታክስ ባለስልጣን የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና ለዚሁ አላማ የተዘጋጀውን ውል በመፈረም ይሆናል፡፡

## 8. የቫውቸሩ ዝርዝር አፈፃፀም

1. የቫውቸሩ ህትመት በባለስልጣኑ የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ይከናወናል፡-
2. የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት የታተሙትን ቫውቸሮች በሰነድ ከባለስልጣኑ ይረከባሉ፡-
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው የማስረከቢያ ሰነድ የቫውቸሩን ዝርዝር መረጃዎች የያዘ ይሆናል፡-
4. የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት ከጫት ላኪዎች በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት ለዚህ አላማ የሚውለውን ውል በማስፈረም ቫውቸሩን ይሰጣሉ፡-
5. ከተለያዩ ክልሎች የጫት ምርት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ላኪ በዋስትና የሚሰጠው ቫውቸር ከየክልሎቹ መውሰድ አለበት፡-
6. የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት ለተጠቃሚዎች የተሰጡትን ቫውቸሮች ቁጥር ከ---እስከ መዝግበው ይይዛሉ፡-
7. የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደ ውጭ የሚልኩት የጫት ምርት ላይ ሊከፈል በሚገባው የታክስ ልክ የተሰጣቸውን ቫውቸር በታክስ መሰብሰቢያ ቦታዎች በማስያዝ የጫት ምርቱን ማጓጓዝ ይችላሉ፡-
8. የታክሱ ሰብሳቢዎች ወደ ውጭ ለሚላክ ጫት ዋስትና እንዲሆን ቫውቸር ሲቀበሉ በቫውቸሩ ላይ በተጠቀሰው የገንዘብ ልክ የገቢ ደረሰኝ ይሰጣሉ፡-
9. የታክሱ ሰብሳቢዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት በሚሰጡት ደረሰኝ ላይም የቫውቸሩን ቁጥር መጥቀስ አለባቸው፡፡

## 9. ቫውቸር የተሰጠበትን የታክስ ሂሳብ ስለማወራረድ

1. የቫውቸር ተጠቃሚ የሆነ ጫት ላኪ በወር ውስጥ ቫውቸር በማስያዝ ከመነሻ ቦታ ያጓጓዘው የጫት ምርት ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን ማስረጃዎች ዋናውንና ኮፒውን በማቅረብ ቫውቸር በዋስትና ላስያዘበት የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣን በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የቫውቸሩን ሂሳብ የማወራረድ ግዴታ አለበት፡-
2. የቀረቡት ማስረጃዎች አግባብ ባለው የክልል የታክስ አስተዳደር ባለስልጣን ከተመረመሩና ሊወራረድ የሚገባው የታክስ ስሌት ከተከናወነ በኃላ የቫውቸር ተጠቃሚው ያስያዘው ቫውቸር እንዲወራረድ ይደረጋል፡-
3. የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣን የማስረጃዎችን ኮፒ ከኦሪጅናሎቹ ጋር በማመሣከር ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጠ በኃላ ተሰልቶ በቀረበው ወደ ውጭ አገር በተላከው ጫት ልክ የቫውቸሩ ተጠቃሚ ያስያዘውን ቫውቸር ያወራርዳል፣

የተወራረደውም “የተወራረደ” የሚል ማህተም ተደርጐበት በክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣን በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡-

4. ላኪው ወደ ውጭ ለመላክ የዋስትና ቫውቸር ሰጥቶበት ያጓጓዘው/ያሳለፈው የጫት ምርት ወደ ውጭ አገር ስለመላኩ የሚያረጋግጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ ካልቻለ ምርቱ ለአገር ውስጥ ገበያ እንደዋለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ታክስ እንዲከፈልበት ይደረጋል፡-
5. ለአገር ውስጥ ገበያ ለዋለው ጫት
   ሀ. ወደ ውጭ መላክ የሚገባው ጫት ሳይላክ ከቀረ ለአገር ውስጥ ገበያ እንደ ዋለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ላኪው በምርቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እና 25% በመቀጫ መልክ በገንዘብ በመክፈል ቫውቸሩን ያወራርዳል፡-
   ለ. ለአገር ውስጥ ፍጆታ በዋለው የጫት ምርት ላይ ከመቀጫው በተጨማሪ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ድረስ ወለድ ታስቦ ይከፈልበታል፡፡

## 10. ቫውቸርን ለማወራረድ የሚቀርቡ ማስረጃዎች

ጫት ላኪዎች ወደ ውጭ ለሚልኩት የጫት ምርት በዋስትና ያስያዙትን ቫውቸር ለማወራረድ ጥያቄያቸውን ለክልሉ ታክስ አስተዳደር ባለስልጣን በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ዋናውን እና ኮፒውን አሟልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡

1/ወደ ውጭ የተላከውን የጫት መጠን በኪሎ እና ዋጋውን፣ ለውጭ ገበያ ሊቀርብ ባለመቻሉ በአገር ውስጥ የተሸጠውን የሚያሣይ በላኪው የተዘጋጀ መግለጫ፣

2/ለውጭ ገበያ እንዲውል የተጓጓዘው ጫት ለውጭ ገበያ መላኩን የሚያረጋግጡ፡-

ሀ.ቫውቸር በዋስትና ሲያሲዝ የተሰጠውን የገቢ ደረሰኝ

ለ.የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣

ሐ.ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣

መ.የማስጫኛ ሰነድ (Bill of Loading/Air way bill)፣

ሰ.የባንክ ፈቃድ፤

## 11. የታተመ ቫውቸር ጥቅም ላይ እስኪውል ተፈጻሚ ስለሚደረግ አሠራር

1/ ጫት ላኪዎች ለታክሱ ክፍያ በዋስትና የሚሰጡት ቫውቸር ታትሞ ስራ ላይ እስኪውል ድረስ በምትኩ ወደ ውጭ እንዲላክ ታክስ ሳይከፈልበት ለሚጓጓዝ ጫት መጠኑ ተጠቅሶ ላኪዎች መተማመኛ እንዲፈርሙ መደረግ አለበት፡፡

2/ ጫት ላኪው እንደ አግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ሲያሟላ መተማመኛው እንደ ቫውቸር ተቆጥሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት የሚወራረድ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. የአሠራር ስርዓት መዘርጋት

የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት የጫት ግብይት፣ የማደራጀት እና የመጫን ስራ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/2/ ላይ በተደነገገው መሠረት በተዘጋጁ ቦታዎች ላይ እየተከናወነ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ታክሱ በወጣው አዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት ስለመሰብሰቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋሉ፡፡

### 13. የሪፖርት አቀራረብ

የክልል ታክስ አስተዳደር ባለስልጣናት፡-

1/ ከጫት የተሰበሰበ የታክስ ገቢ መጠን /በገንዘብና በቫውቸር የተሰበሰበውን በመለየት/፤

2/ ወደ ውጭ ስለመላኩ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ የተወራረደ እና ለአገር ውስጥ ፍጆታ በመዋሉ በገንዘብ የተወራረደ ቫውቸር የገንዘብ መጠን፤

የሚያሣይ ወርሃዊ ሪፖርት ወር በገባ እስከ 20ኛው ቀን ድረስ ለባለስልጣኑ ዕቅድና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት ይልካሉ፡፡

### 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ **መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም**. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

# <u>የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ መመሪያ</u>

## መግለጫ

ስለጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ በሚል የተዘገጀ ረቂቅ መመሪያ ከግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ተዘጋጅቶ አስተያየት እንዲሰጥበት በ13/06/2005 ዓ.ም ለቡድናችን ተልኮ እንዲመረመር ከተመራ በኋላ መመሪያው በአፋጣኝነት እንዲወጣ ስለሚያስፈልግ ረቂቁ ከህጉ ጋር ተገናዝቦ በቡድናችን በኩል እንዲዘጋጅና ለዋና ዳይሬተሩ ቀርቦ እንዲጸድቅ በታዘዘው መሰረት የረቂቅ ስራው ተጀምሮ እለት በእለት ከግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመመካከር በሚከተለው መሰረት ተሰርቶ ተጠናቆ ቀረበ፡፡

1. የመመሪያው መጠሪያ ከግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ስለጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ተብሎ የመጣ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 የታክስ ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል የሚል በመሆኑ የአፈጻጸም መመሪያ ተብሎ የነበረው ተቀይሮ የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ መመሪያ በሚል እንዲስተካከል ተደረገ፡፡
2. ምዕራፍ አንድ በማለት የተጀመረው አወቃቀሩን ለማስተካከል ሲባል ክፍል አንድ እንዲሆን ተደረጎ አጠቃላይ ድንጋጌዎች የሚለው ጠቅላላ በሚል እንዲስተካከል ተደረገ፡፡
3. በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 1 ላይ በአዋጁ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 7/3 የሚለው በተደጋጋሚ አንቀጽ ተባሎ የተገለጸውንና የባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 በመጨመር እንዲስተካከል ተደረገ፡፡
4. የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ ሁለት ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተገለጸው መሰረት መጠሪያው ተስተካከለ፡፡
5. በትርጉም ክፍሉ ውስጥ ታክስ ለሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጉም ለትርጉም አመች በመሆን መልኩ አዋጁን በማስቀደም "ታክስ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 767/2004 መሠረት በጫት ግብይት ላይ የሚከፈል ኤክሳይዝ ታክስ ነው በሚል ተስተካከለ፡፡
6. በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የአዋጁን አንቀጽ መጥቀሱ የማያስፈልግ በመሆኑ እንዲወጣ ሲደረግ በጫት ላይ የሚሰበሰበው ታክስ ክልሎች በጥናት በመለየት ለባለስልጣኑ በሚያሳውቁት ቦታዎች ላይ ብቻ እንዲሆ ተደርጓል፡፡
7. በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ አዋጅ ቁጥር 687/2000 የተባለው ስህተት ስለነበር የባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አወጅ 587/2000 ስለሆነ በዚሁ መሰረት ሲስተካከል በሙሉ አንቀጽ 5ን የአዋጁን አንቀጽ 3 መሰረት ባደረገ እና በመመሪያው አንቀጽ 7/2 ጋር እንዲመሳሰል የታክሱ መሰብሰቢያ ቦታዎች የሚለው ወጥቶ የጫት ምርቱን ከሚያነሱበት በሚለው ቃላ

በመተካትና በክልሎች ስልጣን ላይ ገብቶ ግዴታ የሚጥለውን አገላለጽ በመቀየር እንዲስተካከል ተደረገ፡፡

8. አንቀጽ 8 ውስጥ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 ውስጥ የነበሩ ሀረጎች እራሳቸውን ችለው ንዑስ አንቀጽ እንዲሆኑ ተደርጎ 9 ንዑስ አንቀጽ እንዲኖረው ተደረገ፡፡
9. አንቀጽ አስራ አንድ በሁለት ንዑስ አንቀጽ ተከፍሎ የመመሪያውን አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 8 የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ያሟላ መሆን እንዳለበት ተገልጾ ተስተካከለ፡፡
10. በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 9 ውስጥ ንዑስ አንቀጽ 5 የነበረው ነዑስ አንቀጽ 4 እንዲሆን ሆኖ በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ተዘርዝረው የነበሩት ቅጣቶች ራሳቸውን የቻሉ የፊደል ተራ እንዲይዙ ተደረገ
11. አንቀጽ 12 ላይ ክልሎችን የማዘዝ ሥልጣን ስለማይኖረን የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋሉ በሚለው ለስለስ ያለ ቃል ለመጠቀም ተገደናል፡፡